ለፊደላችን ከፍተኛ ጥንቃቄ እንድናደርግለት ከዚህ በታች ለአብነት የጠቀስናቸው ሊቃውንት አጥብቀው ያሳስቡናል።

፩ ግእዝና አማርኛን ከዕብራይስጥ ከሱርስት፥ ከጽር ሳይቀር እያመሳከሩ ያጠኑ ሊቅ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ

"... የፊደልን ገላ ደፍሮ ለመቁረጥ
ሐኪም መኾን ያሻል በአፍአ በውስጥ፤
አፍአው ዐማርኛ ውስጡም ግእዝ ነው
ትምርቱ እንደገደል ያልተደፈረው።

... ለቋንቋ በሽታ ለጥፊት ሕማም
ከትምርት በቀር መድኀኒት የለም።

... ዐማርኛችንስ በጥፊት ጎዳና
ካባቱ ከግእዝ መቼ ይለይና።

የትምርቱስ ችጋር የውቀቱ ቀጠና
ፊደል በመቀነስ መቼ ይለቅና። ... "

፪ የቅኔ ፈጣሪው፥ የትርጓሜ መጻሕፍት ምስክራቸው
መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ፥

"... ይልቁንም በዐፄ በካፋ ዘመን ሀሌታውን ሀ ከሐመሩ ሐመሩን ሐ ከብዙኃኑ አዛውሮ ጽፎ የተገኘ ጸሓፊ እጹን ይቆረጥ ነበረ ይባላል።
ስለዚህ ቁም ጸሓፊ የሚኾን ሰው ጽሕፈት ሲማር የፊደሎችን አገባብ ቄምር እንጂ ፤ የቅርጻቸውን አጣጣል ማሳመርን ብቻ አልነበረም። ኋላ ግን በቀን ብዛት የመጻሕፍትን ምሥጢራቸውን ሳያውቁ የፊደሎችን አገባብ ሳይጠነቅቁ ፤ የብዕሩን አጣጣል በማሳመር ብቻ የሚራቀቁ በመላ በድፍረት የሚጽፉ ጸሓፍት እየበዙ ስለሔዱ ሀሌታውን ሀ ከሐመሩ ሐ ከብዙኃኑ ኀ ...ሳይለዩ በዘፈቀደ ተዘበራርቀው የተጻፉ መጻሕፍት እየበዙ ሔዱ። ... የግእዙ ሊቅ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ መዝገበ ፊደል በተባለው መጽሐፋቸው፤

ባንዱ የሚጻፈው በሌላው ሲጻፍ
ቋንቋው ተበላሽቶ ይኾናል ጸያፍ
የጸሓፊ ደዌ ያታሚ መከራ
ጠንቅቆ አለማወቅ የፊደልን ሥራ።

እንዳሉት ኹሉ የመጽሐፉ መልክ የፊደሉ አሰካክ ፈጽሞ ስለሚበላሽ እነምን አለበት እነ ኹሉ ቀኙ ያሏቸው ሰዎች ያነቡት እንደ ኾነ እንጂ የፊደሎችን አሰካክ የመጽሐፉን መልክ ያወቀ ሰው ይህን አጻጻፍ ሲያይ ዛብ እንደጨበጠባት በቅሎ ከንባቡ ይገታል እንጂ ሊራመድ አይችልም።

በምሥጢርም በኩል ሠረቀ ተብሎ በንጉሡ ሠ ቢጻፍ ፀሐይ ወይም ኮከብ ወጣ ማለትን ያመለክታል። ደግሞ ሰረቀ ተብሎ በእሳቱ ሰ ቢጻፍ ሌባ ሰረቀ ማለትን ያሳያል። ከዚህ አልፎ ፀሐይ ሰረቀ ሠራቂ ሠረቀ ንዋየ ተብሎ ተጽፎ ቢገኝ ከላይ የተጠቀሱት ሊቅ፤

እንዳገኙ መጣፍ በድፍረት በመላ
የቋንቋ ደረመን የመጽሐፍ ቢስ ገላ
ንባብ የማያሳክክ ምሥጢር የሚቆምጥ
መልክአ ትርጋሜ የሚለዋውጥ

ብለው እንደተናገሩት ምሥጢሩ ፈራሽ ቋንቋው ብላሽ እንጂ ከታሰበው ግብ ሊደርስ አይችልም፤ ይህን የመሰለ ብዙ ነው።"

፫ ግእዝና አማርኛን በገዛ ራሳቸው ስልት ፍርፍር አድርገው የመረመሯቸው አለቃ አፈወርቅ ዘውዴ፥

"በሦስት ፊደሎች በ ሀ፥ ሐ፥ ኀ፥ እና በኹለቱ አ፥ ዐ፥ በኹለቱ ሰ፥ ሠ፥ እና በኹለቱ ጸ፥ ፀ የተነገሩት የግእዙ ቃላት ወደ ዐማርኛው ሲፈቱ፤ እነዚሁ ፊደሎች ሳይለወጡ እንዳሉ ኾነው፥ በዐማርኛው ቃላት ይገኛሉ። ይህም የግእዝ ቃል በሀ ሀላዌ (ሆይ) ሲነገር፥ የዐማርኛውም በሀ ሀላዌ ይነገራል እንጂ፤ በሐ ሐመርና በኀ ብዙ ኃን፤ እንዲሁም የግእዙ ቃል በሐ፥ ኀ ሲነገር፥ የዐማርኛውም በሐ፥ ኀ ይነገራል እንጂ፤ በሀ ሀላዌ አይነገርም ማለት ነው። በቀሩት ፊደሎች ኹሉ ዐዋጁ ይኸው ነው።

... እነሆ ዐይኑ ዐና አልፍ አ፥ ሐመር ሐና ብዙኃን ኀ ከሀላዌ ሀ፥ በድምፅ አሰጣጣቸው የተለዩ እንደነበሩ፥ የታሪክ ሊቆች በሰጡት በቂ ማስረጃ ተገልጧል። (አ. ኪዳነ ወልድ ክፍሌ) ይኽንም ለማረጋገጥ በአንዳንድ አገሮች የምሁራኑ አነጋገር ተጨማሪማስረጃ ሊኾነን ይችላል። ለምሳሌ ከጎጃም ክፍለ ሀገር በቡሬ ዳሞት፥ በደንበጫ፥ በደጋ ዳሞት፥ በአቸፈር፥ በማቻክል፥ በጎዛምን ተወላጆች የኾኑት ምሁራን በጽሐ የሚለውን የግእዝ ስም ሲጠሩት ሐውት ሐመር ሐ ን እንደ ሀላዌ በጕሮሮ እስትን ፋስ ንባብ አይናገሩትም፤ እንደ ከና ቀ ንባብ ከምላስና ከላንቃ መካከል ጋር አጣብቀው ሲናገሩት ይሰማሉ። እንዲሁም በትግሮች አነጋገር በግዕ በሚለው ቃል የዐይኑ ዐ አነጋገር እንደዐረቦች አነጋገር ጕሮሮን ሲመታ ይሰማል። ምክንያቱም አንዳንድ የባቄላ ቅርጣኖች ከፍላት እንደሚወጡ እንዲሁም የቋንቋ ኹናቴ ኹሉ በሌላ ኹናቴ ቢጠፋም ቅሉ፥ ቋንቋው ጨርሶ ስለማይጠፋ ነው። ከዚህም የተነሣ በአውታራቱ ፊደል መንገድ ሀላዌ ሀና አልፍ አ ንባበ እስትንፋስ ሲባሉ፥ ሐመር ሐና ብዙኃን ኀ ዐይኑም ዐ ንባበ ጕርዔ ተብለው ተለይተዋል።"

፬ ግእዝና አማርኛን ማወቅ ብቻ ሳይኾን በዘመናዊውም ሳይንስ የተራቀቁት ፕሮፌሶር ጌታቸው ኃይሌ፥

በዐዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ዐማርኛን በዐማርኛ ለማስተማር የመጀመሪያው ምሁር፥ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ የቅኔ ትምህርት እንዲሰጥም ሐሳብ አቅርበው የነበሩ፤ አሁንም

እሚሰማ ቢኖር ሐሳባቸውን ይደግሙታል ብየ በበኩሌ የማምንባቸው፥ ፕሮፌሶር ጌታቸው ኃይሌ፤ ከኹሉ በፊት በቅርቡ ያሳተሙትን መጽሐፍ ርእሱን እንዴት እን ደጻፉት አጢናችኹ እንድትመለከቱት አሳስባችኃለኹ፥ "ባሕረ ሐሳብ"

ፕሮፌሶሩ፥ በዚሁ መጽሐፍ እንዲህ የሚል ጥልቅ አመለካከታቸውንም ገልጠውል ናል፤ "ይህን መጽሐፍ ያሳተምኩት በባህል በተለየም በቋንቋ ረገድ በመምህራኑና ባ ሁኑ ትውልድ መካከል ያለው ግንኙነት እንዳይቋረጥ ቀጣይነት እንዲኖረው ለማድ ረግ ነው።" የሊህን ምሁር እንዲህ ያለ ድንቅ አብነትነት ያለው ሥራ፤ እኔም በትን ሿ ዐቅሜ ስገመግመው፤ በፈረንጆቹ ቋንቋና የጥናት ዘዴ „Paradigm Shift“ እንደሚ ባለው ላለ ዓይነተኛ ተግባር መንገድ የሚያሳይ ኾኖ አግኝቸዋለኹ፤ ስለዚህም በአ ንድምታ የትርጋሜ ትምህርት ቤት ወደፊት ሊመጣ ለሚችለው እድገት በምሳሌነት ጠቅሼዋለኹ።

"የይስሙላ መምህራን"

"የኢትዮጵያ ቋንቋዎችን ለማጥናትና ለእድገታቸው አጋዥ የሆኑ ተግባራትን ለማ ከናወን የተቋቋመ ተቋም" የካቲት 1993 ዓመተ ምሕረት አንድ የ"አማርኛ መዝገበ ቃላት" አሳትሞ አቅርቦልናል። ከመቅድሙ እንደምንረዳው፤ "አካዴሚው... በሰው ሃይልና ድርጅታዊ ኣቋም ሳይጠነክር በልዩ ልዩ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ላይ ጠቃሚ የሆኑ በረካታ የስነልሳን ጥናቶችን ሊያከናውን" እንደቻለ በማሰብ ራሱን በራሱ ከማ ወደሱም በቀር፥ ስለዐዲሱ መዝገበ ቃላት እንዲኽ ብሏል፥ "በአማርኛ ቋንቋ የእድገ ት ታሪክ ውስጥ ኣንድ ኣቢይ ክንውን እንደሚሆንና በቋንቋው የእድገት ሂደት ውስ ጥም ከፍተኛ ኣስተዋፅኦ እንደሚኖረው የታወቀ ነው።"

ድንቄም አስተዋፅኦ። አበውን ከውሉድ እየለዩ። እንዲያው ለምሳሌ ያኽል፥ ከጊዜ መለኪያዎቻችን እንደነ "ካልኢት" ያሉትን ቃላት አለማካተታቸውን ትተነው፤ የፊ ደል ገበታችንን ኾነ ብለው የጎረዱት መኾኑን ስናይ፤ በ"አካዴሚ"ው ውስጥ የተሰ ገሰጉት፤ አብዛኞቹ "የይስሙላ መምህራን" እንደ ኾኑ ለመገመት እንገደዳለን። ራሳቸውን "አካዴሚ" ብለው መሰየማቸውም ቅሉ፥ ስያሜውን አውጥተው አውር ደው የመረጡት ሳይኾን፥ "ጉባኤ" ማለት ምን ማለት እንደኾነ በሚገባ ያልተረዱ በመኾናቸው፥ ለጽርኡ "አካዴሚ" የዐማርኛ አቻ የሌለው መስሏቸው ሊኾን እን ደሚችል፥ ካዘጋጁልን መዝገበ ቃላት ለመረዳት ይቻላል።

እኛስ እንደዐቅማችን፥ በግእዙ ሀ፥ ሐ፥ ኀ፥ ሰ፥ ሠ፥ አ፥ ዐ፥ ጸ፥ ፀ፥ እና ከ ያሉባቸ ው ቃላት፤ በዐማርኛ በቀጥታ ተወርሰው ስናገኛቸው፥ የግእዙን ሥራት በመከተል መጻፍ እንዳለብን ልናውቅ፤ ወደሌላ ፊደል የሚለወጡትን ደግሞ፥እንደሚከተለው ልንለውጥ ይገባል። የሊቃውንቱን ዐዋጅ በመከተል። ዐዲስ ዐዋጅ ሊያስፈልግም ሊቃውንቱ እንዲደንግጉልን እንጂ፤ በቋንቋችን ማንም እንዳሻው እንዲጫወትበት ማሠልጠን የለብንም።

ከ በ ኸ	ሀ በ አ	ጸ በ ጠ ወይም በ ጨ
	ሐ በ ዐ	ፀ በ ጨ ወይም በ ጠ
	ኀ በ ዐ	

ምሳሌ

ግእዝ	ዐማርኛ
ኮነ ኬደ ወዐልክ፡ ወዐልኩ	ኾነ ኼደ ዋልክ፡ኽ ዋልኩ፡ኹ
ሀገር ሁከት	አገር አውከት
ሐመድ ሕመም	ዐመድ ዕመም
ኀየለ ኀዘነ	ዐየለ ዐዘነ
ጽላል ጽጋግ	ጥላ ጭጋግ
ፀበጠ ፀሓይ	ጨበጠ ጣይ

በዚኽ አጋጣሚ በ"ሳይበር ኢትዮጵያ" የ"ባህልና ሥነ ጽሑፉ"ን ክፍል አስተናባሪ ከልብ አመሰግናለኹ። ይኸውም "ባህልና ስነ ጽሁፍ" የሚል ጽሕፈት ባየኹ ጊዜ፡ እንዲስተካከል ጠይቄ፡ ስለተስተካከለ ነው።